አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር አማላጅና ተማላጅ ሊሆን እንዴት ይችላል? ይላሉ። እግዚአብሔር በልጁ ሥጋና ደም የዘላለም ሕይወት ዋስትና ቃል ኪዳን እንደገባልን ይረሳሉ። «ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ በመጨረሻም ቀን አስነሣዋለሁ» የሚለውን ቃልኪዳን ወደ ጎን ይጥላሉ። ዮሐ.6፡35-59

ዘላለም ማለት እኮ አሥር፣ ሃያ፣ ወይም ሰማንያ ዓመት ማለት አይደለም፤ "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና" የሚለውንም መለኮታዊ የነጻነት አዋጅ ይዘነጋሉ። ሮሜ 8፡1-2።

"እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኮንንስ ማን ነው? የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሳው በእግዚአብሔርም ቀኝ ያለው ደግሞም ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው" በማለት የጸና የአማላጅነት ቃል ኪዳን በክርስቶስ እንዳለን ያረጋግጥልናል። ሮሜ 8፡31-39፤ መዝ.89፡1-3 በማስተዋል ያንብቡ።

መጽሐፍ ቅዱስ፡- "ደም ሳይፈስ ሥርየት የለም" ስለሚል ከክርስቶስ ደም በስተቀር ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቅ የሚችል ሌላ ሕያው አማላጅ የለም። ዕብ 7፡15-28፤ ምዕ 9፡14 ቁ.22 ፩ጴጥ 1፡18-21፤ ሐዋ.ሥራ 20፡28። የመዳን ራስ ኢየሱስ ክርስ ቶስ መሆኑን የሚዘነጉ ሁሉ በቆላስያስ 2፡16 ያለውን የአዲስ ኪዳን መንገድ ይስታሉ። ኤፌ 2፡1-22 በማስተዋል ያንብቡት።

ሐዋርያው ዮሐንስ፡- «ከእርሱ ጋር ሕብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም ነገር ግን



እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፤ ኃጢዓት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢዓታችን ብንናዘዝ ኃጢዓታችንን ይቅር ሊለን ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» ይላል። ፩ዮሐ. 1፡6-10።

"ልጆች ሆይ፤ ኃጢዓትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢዓትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም የኃጢዓታችን ማስተሰሪያ ነው ለኃጢዓታችንም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢዓት እንጂ" በማለት የማይረታ ጠበቃና ዋስ ክርስቶስ እንዳለን በማይዋሽ ቃሉ አረጋግጠልናል። ፩ዮሐ 2፡1-2። «እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባና ወንበዴም ነው» በማለት በሌላ አማላጅ ወደ እግዚአብሔር ቤት መምጣት ፈጽሞ የተከለከለ መሆኑን ያረጋግጣል። ዮሐ 10፡1

ብጽዕት ድንግል ማርያም እንኳን በምድር እያለች በቃና ዘገሊላ ለማማለድ ሞክራ ከኢየሱስ የተሰጣት መልስ፡- «አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?» የሚል ስለነበር «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» አለቻቸው ይላል። ዮሐ 2፡4-5 ስለዚህ ኢየሱስ ያለንን ብቻ ማድረግ ይገባናል።

ኢየሱስ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ብሎ ሌላውን በር በራሱ ዘግቶታል። ዮሐ 14፡6 ሰው ሁሉ ዋስትና ያለው ጠበቃ እያለለት ለምን በከንቱ ይባክናል?

በዮሐ 10፡1-12 ደግሞ፡- በበሩ (በክርስቶስ) ሥጋና ደም በኩል ካልሆነ በቀር በሌላ ፈጽሞ መግባት እንደማይቻልና እርሱን ካልያዙ መዳን እንደሚቀርባቸውም አረጋግጦ አስጠንቅቆአል። በጎቹ ግን በበሩ በክርስቶስ



ሥጋና ደም በኩል የመግባት ዕድል አላቸው። ሰው ሁሉ እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ መሆኑን ረስቶአል።

ቃሉ፡- "አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው (አማላጅ) ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ" በማለት ኃጢአተኛውን ከመለኮትነቱ ጋር የሚያስታርቅ የክርስቶስ ሥጋና ደም በመካከላችን እንዳለልን አረጋግጦልናልና፤ ሳናወላውል በቃሉ ታምነን ልንድንበት ይገባል።

አንዳንድ ሰዎች መላዕክት ስለሚያማልዱ ልመናና ስግደት ሊቀርብላቸው ይገባል ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ፦ እያንዳንዱ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው፣ ያለምንም ልመና መልአክ በአጠገቡ እንዳለውና ከክፉ ነገር ወይም ከሰይጣን እንደሚታደገው ይናገራል። ማቴ 18፡10፤ መዝ 34፡7። 19፡1-16፤ ዘካ 3፡1-10። ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ምዕመኑ እግዚአብሔርን የሚወድና የሚፈራ አንድ አምላክንም ብቻ የሚያመልክ ስግደትም ለአንድ አምላክ ብቻ መሆኑን የሚያምን የሆነ እንደሆን ብቻ ነው። ኢሳ. 42፡8፤ ዘካ 3፡1-8፤ መዝሙር 34፡6-10፤ ሐዋ.ሥራ 5፡17-21፤ ምዕ 12፡6-11 መላእክት ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ያውቃሉና፤ መላእክት እንዲሰገድላቸው አይፈቅዱም። ራእይ 19፡9-10፤ ምዕ 22፡8-9። መላዕክት የንስሐ ልብ የሌለውን ኃጢዓተኛ አይወዱም። እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ሊቀስፉ ሲልካቸውም አይምሩም። ፩ነገ.19፡35-37፤ ሐዋ.ሥራ 12፡23። መላእክት፦ እኛ እውነተኞች የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስንሆን ከእግዚአብሔር ተልከውልን የሚረዱን ከአደጋም የሚጋርዱን ረዳቶቻችን ናቸው። መዝ 91፤ ዕብ 1፡14። ከመለኮት ጋር የማስታረቅ ቃል ግን በወንጌል በኩል በክርስቶስ